# ፍትሕ የጠማው ህዝብ

## ለጋራ ችግር በጋራ ለመፍታት አብረን እንነሳ!!

ክፍል አራት
(የመጨረሻው)

ከይኩኖ መስፍን
ቦስተን/አመሪካ

### ኋላ ቀር አመለካከትን ሰብረን ለመውጣት ትግሉ ከራሳችን ይጀምር

ባለፉት ጥቂት ቀናት **"ፍትሕ የጠማው ህዝብ"** በሚል ዓቢይ ርእስ ከአንድ እስከ ሶስት ተከታታይ ክፍሎች ለንባብ አቅርቤ እንደነበር ይታወሳል። አዎ!! ችግሩ ከመቼውም ጊዜ እየተባባሰ መምጣቱ እሙን ነው። ሕብረተሰቡ አፍነውና አሸብረው ከመግዛት ባሻገር በረሃብ አለንጋና በንሮ ውድነት የሚላስ የሚቀመስ አጥቶ በሆዱ እየተቀጣ የሚገኘው ወገን ቁጥሩ ቀላል እንዳልሆነ፣ የህወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች የኢትዮጵያ ህዝብ ለያይተው፣ አደናግረው፣ አደንቁረውና አሸብረው ዘላለም ለመግዛት በዜጎቻችን ላይ እየወሰዱት ያሉት የአፈና ተግባራት ምን ያህል ዘግናኝና አሰቃቂ እንደሆነ ቀደም ብዬ ባቀረብኩዋቸው ተከታታይ ፅሑፎቼ በዝርዝር ተጠቀሷል።

ወደ ዝርዝር የዛሬው ጉዳይ ከመግባቴ በፊት በዚሁ አጋጣሚ ፅሑፎቼን ለንባብ እንዲበቁ የተባበራችሁኝ ድሕረ ገፆች፣ ሬድዮኖች፣ ቴለቪዥኖች፣ ፓል ቶኮችና እንዲሁም ገንቢና አበራታች አስተያየታችሁን በኢሜል በኩል የላካችሁልኝ ውድ ወገኖቼ ሁሉ ከፍ ያለ ምስጋናዬን በያላችሁበት ይድረሳችሁ እላለሁ። በተጨማሪም በሀገር ውስጥም ሆነ በባሕር ማዶ የምትገኙ ኢትዮጵያውያን ወንድሞቼና እህቶቼ ሁሉ እንኳን ለ2012 የፈረንጆች አዲስ ዓመት አደራሳችሁ እላለሁ። ዓመቱም ያለፈውን ለታሪክ ትተን አንድነታችንንና ሕብረታችንን የምናጠናክርበትና አዲሱ ዓመት አዲስ የታሪክ ምዕራፍ የምንከፍትበት ዘመን እንዲሆንልን ከልብ እመለኛሁ።

የዛሬው አራተኛውና የመጨረሻ ክፍል ፅሑፌም በዋናነት የሚያተኩረው በመፍትሔው ዙሪያ ሲሆን በሀገራችን እየታየ ያለው መቋጫ የሌለው ችግር በመሰረቱ ሊፈታ የሚችለው በተወሰኑ ዜጎች ትግል ብቻ ሳይሆን ህዝቡ ራሱ የጉዳዩን ባለቤት ሆኖ ሲገኝ ነው። ስለሆነም በሀገርና በህዝብ ላይ ያንጃበበውን አደጋ በመንሲኤውም ሆነ በመፍትሔው ቀጥተኛ የሆነ ሃላፊነት አላቸው ብዬ ያመንኳቸውና በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ያገባናል ለሚሉ ወገኖች ሁሉ የሚከተለውን ወቅታዊና አንገብጋቢ ጥሪን አስተላልፋለሁ።

### 1. ለህወሓት/ኢሕአዴግ ደጋፊዎችና አባላት በሙሉ

ማንኛውም በሀገሬ ጉዳይ ላይ ያገባኛል የሚል ሰው በመከባበር፣ በመደማመጥና በመቻቻል ላይ የተመሰረተ፣ የሰለጠነ ልዩነት ይዞና የሌላውን መብት አክብሮ የፈለገውን ለመቃወም ወይም ለመደገፍ ዲሞክራሲያዊ፣ ሕገ መንግስታዊና ዜግነታዊ መብቱ ነው የሚል ፅኑ እምነት አለኝ። የመንግስት ደጋፊ ወይም የህወሓት/ኢሕአዴግ አባልና ደጋፊ የሆነ ሁሉ ጠላቴ ነው የሚል ጭፍን አመለካከትም የለኝም። የኔ እምነትና አመለካከት ካልደገፋችሁ ጠላቶቼ ናችሁ በማለት የሌሎችን ዜጎች ሰብኣዊ ነፃነት የምጋፋ ሰውም አይደለሁም። በዜጎች ላይ በጥላቻ፣ በቂም በቀልና በግል ወይም በቡድናዊ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ተቃውሞም የለኝም። በስርዓቱና በደጋፊዎቹ ላይ ያለኝን ልዩነት ወይም ተቃውሞ በሀገርና በህዝብ ጉዳይ ላይ የተመሰረተ ብቻ ነው። በመሆኑም በህዝብና በሀገር ላይ ለሚደርሰው በደል ሕግና ስርዓት አክብሬ በሰላማዊ መንገድ በመቃወሜ ወይም በመፃፌ ብቻ የሚሰነዘርብኝ ጥቃት፣ ስም ማጥፋትና መታሰር ካለም ለመቀበል ዝግጁ ነኝ ብዬ ወስኜ የገባሁበት ነገር ነው። በዚች ምድር ከሀገሬና ከነፃነቴ በላይ የማስቀድመው ጥቅምና የምፈራው ሀይል ፍፁም የለኝም ብዬ አምናለሁ።

ስለሆነም ዛሬ በዚህች ፅሑፌ ለናንተ የስርዓቱን አባላትና ደጋፊዎች ለማስተላለፍ የፈለግኩት አጭር መልእክት እንደሚከተለው ነው። እሱም "የምታራምዱት ፓሊሲ፣ የምትወስዱት እርምጃና የምትከተሉት አመለካከት ለሀገርና ለህዝብ አይበጅም ብቻ ሳይሆን ለናንተ ለራሳችሁም የማይጠቅም የጥፋት መንገድ ስለሆነ ከዚህ አፍራሽ ተግባር ታረሙ" የሚል ነው። በመሆኑም የህወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ለዓመታት ያህል በደጋፊዎቻቸውና በአባላቶቻቸው አእምሮ ላይ የተከሉዋቸው መታረም አለባቸው ብዬ ያመንኩዋቸው ፀረ አንድነት፣ ፀረ ዕድገትና ፀረ ዲሞክራሲ ከሆኑት ኢ ሰብኣዊና ኋላ ቀር አመለካከቶች ውስጥ የሚከተሉትን ነጥቦች በአጭሩ ልጥቀስ።

ሀ) <u>የትግራይ ህዝብና ህወሓት አንድ ናቸው</u> ብለው የሚያምኑና በጭፍን የሚሰብኩ የህወሓት አባላትና ደጋፊዎች ጥቂቶች አይደሉም። የድርጅቱ አባላትና ደጋፊዎች ገና በወጣትነታቸው ጀምሮ ሌላ አማራጭና ነፃ ሃሳብ እንዳይኖራቸው በዚሁ ኢ-ዲሞክራሲ በሆነ አመለካከት ታንፀውና ተኰትኩተው እንዲያድጉ ተደርጓል። ይህ የተዛባ አመለካከትም ረጅም ታሪክና አኩሪ ባህል ያለው ህዝባችን ህወሓት ሲፈጠር አብሮ የተፈጠረ ህወሓት ከሌለ ደግሞ አብሮ የሚጠፋ በማስመሰል የአንድ ድርጅት ንብረትና አገልጋይ አድርጎ መፈረጅ ክብሩን ነፃነቱንና ማንነቱን የሚያሳንስ ብቻ ሳይሆን በዲሞክራሲ መርህ አኳያ ሲታይም ከሳይንስና ከህቅ ውጭ ነው። በተለይም ለነፃነትና ለዲሞክራሲ ታግለናል በምትሉ መሪዎችና ካድሬዎች አፍ ሲነገር መስማቱ በጣም የሚያሳዝንና የሚያሳፍር ነው። ይህ የሚያሳየንም የህወሓት ካድሬዎችና ደጋፊዎቻቸው ዲሞክራሲና የብዙሃን ፓርቲ ስርዓት የሚል የታገሉለት አላማ ብቻ ሳይሆን በሕገ መንግስቱ ቁልጭ ብሎ የሰፈረ አባባል ቃሉ እንጂ በተግባር ምን እንደሆነ የማያውቁት መሆናቸው መገንዘብ ይቻላል። ስለዚህ መንግስትና ህዝብ (ድርጅትና ህዝብ) ለይቶ ማወቅና መታገል ቀለም መቁጠር ወይም የግድ የፓለቲካ ሳይንትስት መሆን የሚጠይቅ አይደለም። የሚጠይቀው ቅንነት፣ ሚዛናዊነትና የህዝብ ወገንተኛ መሆንና አለመሆን ብቻ ነው። ቀበሮና ፍየል ለይቶ የማያዉቅ እረኛ ከጅብ አያድንምና።

ለ) የህወሓት መሪዎች በደጋፊዎቻቸው አእምሮ ላይ ከዘሩት ሌላው መርዘኛ ፕሮፓጋንዳ በኢትዮጵያ ውስጥ ከህወሓት የተለየ አመለካከት ይዞ የተደራጀ ሌላ የፓለቲካ ድርጅት <u>እንደ መብት ሳይሆን እንደ ጠላት መፈረጅ</u> ነው። ይህም ለዓመታት ስር የሰደደ ትልቁ በሽታና አደገኛ አመለካከት ነው። ከዚህ በመነሳት ትምክሕተኛ፣ ነፍጠኛ፣ ደርግ-ኢሰፓ፣ ኦነግ፣ ሻዕቢያ፣ ወዘተ በማለት ታርጋ ይለጠፍበታል። ይህም ከሁለት ነገሮች የሚመነጭ ነው። አንዱ ጠንካራ የሆነ ሌላ የፓለቲካ ድርጅት በኢትዮጵያ ምድር እንዳይበቅል ለመኰርኰምና ለመመንጠር እንዲመች ሲሆን ሌላው ምክንያት ደግሞ ካድሬዎቻቸውና ደጋፊዎቻቸው ያለ እነሱ ጀግና፣ ለሀገሩ አሳቢና ጥብቅና መቆም የሚችል ሌላ ኢትዮጵያዊ እንደሌለ አስመስሎ ለማቅረብ ሲሆን ትግርኛ ተናጋሪ ሁሉ በሌሎች ኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ላይ ንቀት፣ ጥርጣሬ፣ ስጋትና ጥላቻ እንዲያድርበት በማድረግ በዓይነ ቁራኛና በፍርሃት ተውጦ ሰጥ ረጭ ብሎ ለአንድ ድርጅትና ለጥቂት መሪዎች አሜን ብሎ እንዲገዛ ለማድረግ ነው።

ይህ ዓይነቱ ፕሮፓጋንዳ ከአቶ መለስ ዜናዊ ጀምሮ በየደረጃው ያሉት የህወሓት ካድሬዎች በተለይም በትግርኛ ቋንቋ በስብሰባም ሆነ በብዙሃን ዜና ማሰራጫዎች የሚናገሩት መሆኑን ዋቢ የሚያስፈልገው አይደለም። ለምሳሌ በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ2002ዓ.ም ምርጫ ዋዜማና በህወሓት 37ኛው የልደት በዓል ምክንያት በማድረግ በትግራይ በመቀሌ ከተማ ተገኝተው ለትግራይ ህዝብ ያስተላለፉት የክተት መልእክትና በተከታታይ ያደረጉት ቃለ ምልልስ ልብ ብሎ ላጤነውና ለተከታተለው ሰው ከላይ የተጠቀሰውን አመለካከት የሚያረጋግጥ ነው።

ሐ) የስርዓቱ መሪዎችና ካድሬዎቻቸው ስልጣን በሞኖፓል ይዘው ዘላለም ለመኖር የሚጠቀሙበት ሌላው ፀረ ዲሞክራሲና ፀረ አንድነት የሆነ የማስፈራሪያ ስልት <u>"እኛ በረሃ ወጥተን መስዋእትነት ከፍለን</u>

ታግለን ያመጣነው ለውጥ ማን ይጋራናል" የሚል ነው። እነሱ ነፃ አውጪ ሌላው ኢትዮጵያዊ ደግሞ የነሱ የነፃነት ተስፈኛ፣ እነሱ የተለዩ ጀግኖች ሌላው ወገን ፈሪ፣ እነሱ የነፃነት ሃዋሪያ ሌላው ደግሞ ለባርነት የተፈጠረ በማስመሰል ሀገሩን በደሙ ጠብቆ ያቆየ የኢትዮጵያ ህዝብ ጀግንነትና ክብር የሚያንቋሽሽና የሚያሸማቅቅ ተግባር ሲሰሩ ይታዩሉ። ከዚህ የተነሳ የዜጎች የነፃነት አከፋፋይና ቸርቻሪ በመሆን እነሱ ሲፈልጉ የሚቸሩህ ካልፈለጉ ደግሞ የሚነጥቁህ የህወሓት ስጦታ ተደርጎ የሚወሰድበት ጊዜ ላይ ነው ያለነው። በዚህ ምክንያት "እኛ ስንታገል የት ነበራችሁ?" እየተባሉ የግል ስብእናቸውንም ጭምር በሚዳፈር መልኩ በተወለዱባት ምድር ተዋርደው የሚኖሩ ዜጎች ጥቂቶች አይደሉም። ለነገሩ የኢትዮጵያ ህዝብ ታጋሽ፣ ይቅር ባይና ሆደ ሰፊ ሆነ እንጂ ትናንት ከሻዕቢያ ጎን ተሰልፎ ሀገርንና ወገንን ሲያደማ የነበረ፣ የህዝብ ሉዓላዊነትና ክብር በባዕድ ድርጅት ያስደፈረ፣ ብሄራዊ ጥቅማችንን ለባዕድ አሳልፎ የሸጠ፣ ኢትዮጵያን ያለ ባህር በር ሽባ ሆና እንድትቀር ያደረገ ድርጅትና መሪ የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃ አውጪ ነኝ ብሎ መፎከርና በሌሎች ዜጎች ላይ ጣት ለመቀሰር ምን ያህል የሞራል መሰረትና ብቃት ይኖራቸዋል? የሚል ጥያቄና ትዕዝብት በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ አእምሮ ሊኖር እንደሚች አልጠራጠርም። ስለዚህ ጠባብ፣ ኋላቀርና ሞኖፓላዊ አመለካከት በጊዜው ካልታረመ እየዋለ እያደረ ሲሄድ የሚያመጣው ጣጣ ቀላል አይሆንም።

መ) የትግራይ ተወላጅ ሆኖ የህወሓት ፓሊሲ መቃወም፣ የሌላ ድርጅት አባል ሆኖ ለኢትዮጵያ ሀገሩ መታገል፣ ህወሓትን የሚነቅፍ ፅሑፍ መፃፍ ወይም በዜና ማሰራጨት፣ ለጠባብ ድርጅት አልገዛም ብሎ ነፃ ሰው ሆኖ ለመኖር ማሰብ ማለት በመሪዎቹና ካድሬዎቻቸው ዘንድ እንደ ሃጢአተኛ፣ ከሃዲ፣ ጠላትና ወንጀለኛ ያስቆጥራል። ከድሮ ሲፈጠሩ ጀምሮ የጠረጠሩትን ሰው ሰበብ አስባብ እየፈለጉ ከሕብረተሰቡ እንዲገለል ከማድረግ ባሻገር የሸዋ ትግሬ፣ የነፍጠኛና የትምክተኛ ወኪልና አሽከር እየተባለ በማንነቱ እንዲያፍርና እንዲሸማቀቅ ይደረጋል። የመጨረሻ ዕድሉም መታፈን ወይም ሀገሩን ለቆ መሰደድ እንደሆነ ባለፉት ተከታታይ ፅሑፎቼም በዝርዝር ተጠቅሷል። በተለይም ለህወሓት ያልተንበረከኩና መሳሪያ ያልሆኑ የትግራይ ምሁራን በትግሉ ድርሻ እንዳይኖራቸው አንገታቸው እንዲደፉና እንዲሸማቀቁ በመደረጋቸው ጠባሳው እስካሁን ድረስ ለመብታቸው እንዳይታገሉ በያሉበት የጋን መብራት ሆነው እንዲቀሩ ምክንያት ሆኗል። ዛሬም ህወሓትን የሚያጋልጥ መፅሐፍ ፅፋችሁ የትግራይን ጉዳይ ለሌላው ባዕድ አሳልፋችሁ ሰጣችሁ ተብለው በወህኒ ቤትና በፍርድ ቤት የሚንገላቱ ወገኖች ጥቂቶች አይደሉም። ለምሳሌ የህወሓት አንጋፋ ታጋይ ነበር አቶ አስገደ ገብረስላሴ የጥቃቱ ሰለባ ከሆኑት ሰዎች አንዱ ናቸው። የቀረበላቸው ክስም በእጅ አዙር በአቶ ብስራት አማረ የሚመራ ቡድን ራሱ ከሳሽ፣ ራሱ መስካሪና ራሱ አሳሪ በመሆን የተቀነባበረ ሴራ መሆኑን በተለያየ ዜና ሰምተኗል። የሚገርመው ነገር!! አቶ አስገደ መከሰሳቸው ብቻ ሳይሆን በሀገርና በወገን ላይ ግፍና በደል የፈፀሙ ሰዎች ከሳሽ የሚሆንበት፣ በአንፃሩ ለሀገራቸውና ለህዝባቸው ጥብቅና የቆሙ ዜጎች ግን እንደ ወንጀለኛ ተቆጥረው የሚከሰሱበትና የሚንገላቱበት ጊዜ ላይ መድረሳችን ነው።

ሰ) ሌላው የህወሓት መሪዎችና ደጋፊዎች ፀረ ዲሞክራሲና ፀረ ፍትህ አመለካከት እንደ ድርጅት ወይም እንደ የፓለቲካ ሰዎች በሀገርና በህዝብ ላይ የፈፀሙትን በደል ለጥቂት መሪዎችና ካድሬዎች መቃወም ማለት ለትግራይ ህዝብ መሳደብ ወይም መድፈር አድርገው ይቆጥሩታል። በዚህ ምክንያት ህዝብን ተሳድብሃል ወይም ደፍረሃል እየተባለ አፉ እንዲይዝ ወይም በጠላትነት እንዲፈረጅ ይደረጋል። ይህ ዓይነቱ ፕሮፓጋንዳ ደግሞ ከሁለት ነገሮች የሚመነጭ ነው። አንዱ ህወሓትና የትግራይ ህዝብ አንድ ናቸው የሚለው አመለካከት የወለደው ሲሆን ሌላው ደግሞ ለትግራይ ህዝብ ያሰቡና የተቆረቆሩ በመምሰል እነሱ የፈፀሙትን ወንጀል የትግራይ ህዝብም እጅ አለበት እንዲባልና ከነሱ ጋር ተደምሮ አብሮ እንዲወቀስ እንደ ሽፋንና ከለላ አድርገው ለመጠቀም ነው።

ወገኖቼ ሆይ!! እውነታውና ሀቁ ይህ ከሆነ!! የህወሓትና የመንግስት ደጋፊዎች ነን የምትሉ ሰዎች ሁሉ እውነት ጥብቅናችሁ ለህዝብና ለሀገር ከሆነ፣ የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጪ ከሆናችሁ፣ የታገላችሁት ለዲሞክሲ፣ ለሰው ልጅ መብትና ነፃነት ከሆነ፣ ለኢትዮጵያ ህዝብ እኩልነት የምታስቡ ከሆነ ታዲያ!! በሰላማዊ መንገድ ለሕግ የበላይነት፣ ለሰብኣዊ መብትና ዲሞክራሲ በሚታገሉ ወገኖች ላይ ኢ ሰብኣዊ የሆነ በደል ሲፈፀም በአደባባይ በግልፅ እያያችሁና ሕሊናችሁን እየተገነዘበው ለምን የወንጀሉን ተባባሪና አራማጅ ትሆናላችሁ?። በረሃ ወጥተው ከጠላት ጋር ሲፋለሙ በአሰርተ ሽዎች የሚገመቱ ለጋ የትግራይ ወጣቶች የተሰውለት አላማ ለዚህ ነበር ወይ?። እናንተ በተለይም የህወሓት አባላትና ደጋፊዎች የሆናችሁ ሁሉ ትግላችሁና ድካማችሁ አንድ ፈላጭ ቆራጭና ከሕግ በላይ የሆነ መሪ ብቻ ዘላለም ለማንገስ ነበር ወይ?። በረሃ ወጥታችሁ ግንባራችሁን ለጥይት ያልሳሳችሁ ታጋዮች ዛሬ በሰላማዊ መንገድ ሕግ ይከበር!! በደለኛ ለፍርድ ይቅረብ!! ጭቆናችን ገደብ ይኑረው!! ብላችሁ ለመናገር አፋችሁ የተሸበበው በምንድን ነው?

አዎ!! የእሳት ልጅ አመድ!! እንዲሉ እንደነ አሉላ አባ ነጋ፣ አፄ የሐንስ፣ ሓየሎም አርአያና ሌሎች በሽዎች የሚቆጠሩ ጀግኖች ታጋዮች የተወለዱባትና የተቀበሩባት የትግራይ ምድር ዛሬ ባለቤት አጥታ የህዝብን መብትና ነፃነት ይከበር ስላሉ ብቻ ውድ ልጆችዋን እንደ ጠላት ሲፈረጁ፣ ቤታቸው በቦብ ሲቃጠል፣ እንደ እንስሳ በአደባባይ በዱላ ተደብድበው ዓይናቸው ሲጠፋ፣ ቤታቸው ሲቦረቦር፣ እንደ ሁለተኛ ዜጋ ተቆጥረው ሲንከራተቱ፣ ሲታፈኑ፣ ሲሰደዱ፣ የሀገርና የህዝብ ሃብት በጥቂት መሪዎችና ካድሬዎች ሲዘረፍ፣ ጥቂት መሪዎች ከሀገርና ከሕግ በላይ ሆነው ሉዓላዊነትዋን ሲቸረችሩና በወገን ላይ ሲቀልዱ፣ አድልዎ ሲፈፀምና ሕግ ሲጣመም በግልፅ እየታየ ዝም ማለቱ ምንድን ነው?። ዛሬ ትግራይ በሰራዊትና በካድሬዎች ጋጋታ ተጨንቃ የአፈና፣ የፍርሃት፣ የሽብርና የርስ በርስ መበላት ተምሳሌት ሆና "ሰሜን ኮሪያ" እየተባለች ስትጠራ ጀግኖች ሰማእታት ልጆችዋ ከመቃብር ተነስተው ዛሬ ቢያይዋት ምን ይሉ ነበር?። በገዛ የራስህ ወገን መቃብር ላይ ቆሞ ቤት እየሰራ፣ አንዱ በባርነት ሌላው በነፃነት እየኖረ፣ አንዱ በጨለማ እስር ቤት ሲማቅቅ ሌላው በሙስና እየተጨማለቀ ዶልቶት እየኖረ፣ አንዱ በረሃብ አለንጋ እየተገረፈ ሌላው በአቋራጭ ፎቅ ሰርቶ ሲንደላቀቅ ባለበት ሁኔታ ላይ ሆነን እውነት ዘላቂ ሰላም፣ ዕድገትና ልማት ሊረጋገጥ ይችላል ብላችሁ ታምናላችሁን?። ሰላምና ፍትሕ ከሌለስ የሚተከሉት የልማት ተቋማቱ ዋስትና ሊኖራቸው ይችላልን? መልሱ፣ ፍርዱና ውሳኔው ለናንተ ትቸዋለሁ።

## 2. ለተቃዋሚ ሀይሎችና ታጋይ ወገኖች

ቀደም ሲል ባቀረብኩዋቸው ተከታታይ ፅሑፎቼና በዚሁ ከላይ በቁጥር 1 በዝርዝር የተጠቀሱትን የስርዓቱ ደጋፎዎችና አባላቶቻቸው የሚያራምድዋቸው ፀረ አንድነት፣ ፀረ ዲሞክራሲና ፀረ ፍትሕ የሆኑ እርምጃዎችና አመለካከቶች ስርዓቱ የዘረጋቸው የችግሩ አካል መሆናቸው ግልፅ ነው። ይሁን እንጂ እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ትልቁ ጥያቄ ከዚሁ ዓይን ያወጣ ጭቆናና መከራ ለመዉጣት ከያንዳንዳችን የሚጠበቅ የትግል ድርሻ ምንድን ነው? የህወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎችና ጀሌዎቻቸው ስልጣን ላይ ለመቆየት የሚያስችላቸውን ነገር ሁሉ ሳይተኙ ሌት ተቀን ይሰራሉ። እኛስ? በሀገራችን ነፃነት፣ ፍትሕ፣ የሕግ የበላይነትና ዲሞክራሲ እንዲኖር የምንመኝና ለለውጥ የምንታገል ሰዎች ወቅቱ፣ ህዝቡ፣ ሁኔታውንና ትግሉ የሚጠይቀውን ስራ በትክክል እየሰራን ነው ወይ? ላለፉት በርካታ ዓመታት ሲካሄዱ የቆዩ የተናጠል ትግሎችና የተከፈለው መስዋእትነት ለምን ውጤት አላመጣም? አሁንስ ካለፈው ተመኩሯችንና ውድቀታችን ምን ያህል ተምረናል? ለቀጣዩስ ምን ያህል ተዘጋጅተናል?። ለመሆኑ በስልጣን ላይ ያለው ስርዓት መሰሪ ባህርይና ተንኰል ጠንቅቀን የምናውቅና ለሱ የሚመጥን ራእይ ይዘን ትግል የምናካሂድ ስንቶቻችን ነን? የሚሉና ሌሎች ጉዳዮች ቀጥለን የምናያቸው ናቸው።

## ሀ) ኋላ ቀር የፓለቲካ አመለካከትና የቅራኔ አፈታት ባህል ሰብረን ለመውጣት ትግሉ ከራሳችን ይጀምር

እኛ ኢትዮጵያውያን ዋናው ችግራችን የኢኮኖሚ ድህነት ብቻ አይደለም። የአመለካከት ድህነትም በሕብረተሰባችን ዘንድ ስር ከሰደዱ ችግሮች አንዱ ነው። ይህ ኋላቀር የፓለቲካና የቅራኔ አፈታት ባህላችን በስልጣኔና በዕድገት ጎዳና ላይ አንድ እርምጃ ወደፊት እንዳንራመድ ለዘመናት ጠፍሮ ይዞን ቆይቷል። የህዝብንና የሀገርን ጉዳይ ማእከል ያደረገ ልዩነት ይዞ በሰለጠነ መንፈስ አብሮ መስራት፣ ቅራኔ በሰለጠነ መንገድ በጠረጴዛ ዙሪያ መፍታት፣ ያለፈውን ለታሪክ ትቶ ከስህተቱ ተምሮ ይቅር ብሎ ስለነገ ማሰብ፣ በጋራ ችግር ላይ በጋራ መስራት፣ ወዘተ የመሳሰሉትን የአንድ የሰለጠነ ሕብረተሰብ ባህል፣ የዕድገትና የዲሞክራሲ መለኪዎች ናቸው። ይሁን እንጂ በኛ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ብዙ የተለመዱ ባህሎች አይደሉም። አብዛኞቹ በመካከላችን የሚከሰቱ ቅራኔዎች በሀገርና በህዝብ ጉዳይ ላይ ሳይሆን በስልጣን ሽኩቻና በጠባብ ቡድናዊ ጥቅም ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ይህ በመሆኑም ልዩነት ይዞ በጋራ ጉዳይ ላይ በጋራ ከመስራት ይልቅ መናቆር፣ እርስ በርስ መጠላለፍ፣ ስም መጠፋፋትና በጠላትነት ዓይን መታየት ያደላሉ።

ኋላ ቀር የፓለቲካና የቅራኔ አፈታት ባህላችን መገለጫ ከሆኑት ችግሮቻችን አንዱ ከስህተታችን አለ መማር ነው። ከዚሁ ጋር የተያያዘ የአንድ ጀርመናዊ ፈላስፋ አባባል ልጥቀስና ወደ ዋናው ነጥቤ ልመለስ። "አንድ ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ ከአሳሳተኝ ስህተቱ የኔ ሳይሆን የሰውዬው ነው። ሁለተኛ ጊዜ ካሳሳተኝ ግን ስህተቱ የሰውዬው ሳይሆን የኔ ነው" ይላል። አዎ!! በታሪካችን በተለይም ከአፄ ኃይለ ስላሴ ህልፈት በኋላ ብዙ ውጣ ውረድ አልፈናል። ህወሓት/ኢሕአዴግ ስልጣን ከያዘ በኋላም ብዙ ነገሮች ተቀያይሯል። በዚሁ የትግል ሂደት 1997 ዓ.ም ሀገራዊ ምርጫን ጨምሮ ብዙ ወርቃማ ሁኔታዎች ከእጃችን አምልጠውብናል። አሁንም ገና ከስህተታችን የተማርን አይመስለኝም። ከስህተት መማር ማለት ለበለጠ ጥንካሬና ብቃት አድርጎ ከማሰብ ይልቅ እንደ ውርደትና እንደ ድፍረት የሚቆጥሩት የፓለቲካ መሪዎች ጥቂቶች አይደሉም። ለምሳሌ አንዳንድ የፓለቲካ ስብስቦች ሌላ አማራጭ መንገድ ማየት አቅቷቸው ድርጅታቸው እንደ ቅርስ ሙጡኝ ብለው በመያዝ ለአርባና ለሃምሳ ዓመታት ያህል አንድ ዓይነት ስህተት ደጋግመው ሲሰሩ ይታያሉ። በአንፃሩ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ደግሞ የነሱ ስህተት የበለጠ ሲጠቀምበትና ሲማርበት ይታያል።

እውነቱን ለመናገር አንዳንድ ድርጅቶች ስህተት አላችሁና ከድክመታችሁ ታረሙ ብሎ ለመናገር በጣም አስቸጋሪ ነው። ስህተት አለህ ብሎ መናገር ለመንግስት ብቻ እንጂ ለፓለቲካ ድርጅት የማይመለከት አድርገው የሚገነዘቡ ፓለቲከኞች ጥቂቶች አይደሉም። ደፍረህ ሂስ ብታቀርብላቸው ደግሞ "ሞኝ ከመካሪው ጋር ይጣላል" እንደሚባለው ልክ እንደ መንግስት ካድሬዎች በተመሳሳይ ስማ ስም በመለጠፍ ባንተ ላይ ይዘምታሉ። በስም ማጥፋት የተካኑ ደግሞ ለራሳቸው አንድ እርምጃ ወደፊት እንኳን መራመድ ያቃታቸው ዕድሜ እየቆጠሩ ጊዜና ትውልድ የጣላቸው "ቆማ ቀረች" እየተባሉ የሚጠሩና የፓለቲካ ድርጅቶች ነን እያሉ ራሳቸውን እያፅናኑ የሚኖሩ ናቸው።

ስለዚህ ትግሉ ከራሳችን ካልጀመረና ራሳችንን ማሸነፍ ካልቻልን የ16ኛው ክፍለ ዘመን ኋላ ቀር የፓለቲካ አመለካከትና የቅራኔ አፈታት ባህል ይዘን በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን አስተሳሰብ ላይ ላለው ሕብረተሰብ መምራት እንደማንችል ማመን አለብን።

## ለ) እውነታን ለመቀበል የሞራል ብቃትን፣ የፓለቲካ ብስሌትንና ህዝባዊ ወገንተኝነትን ይጠይቃል

በትምህርት ዓለም እውነታን መቀበል ማለት ሳይንስን መቀበል ይሆናል። በፓለቲካ ዓለምም እውነታን መቀበል ማለት ከጊዜ ጋር መራመድ ወይም ትክክለኛውን አማራጭ/ሀቅ መቀበል ማለት ይሆናል። እስካሁን ድረስ በተከፈለው መራራ መስዋእትነትና በተደረገው ተደጋጋሚ እንቅስቃሴ ትግሉ አንድ እርምጃ ወደ ፊት እንዳይራመድ መሰናክል ሆነው ከቆዩት ነገሮች አንዱ እውነታን የሚቀበል ባህርይ፣ ልምድና ባህል ስለሌለን ነው። በተለይም በውጭ ሀገር የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ነን የሚሉ ፅንፈኛ ድርጅቶች የሚያራምዱትን ፓለቲካ ከዚህ ጭፍን አመለካከት የፀዳ አይደለም። ለርካሽ የፓለቲካ ጠቀሜታ ሲባል ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የሚያሰራጭዋቸው ፕሮፓጋንዳዎች በሀገራችን ካለው እውነታ ጋር ሲነፃፀሩ የሚቃረኑ ናቸው። በባህላችንም፣ በታሪካችንም ሆነ በልምዳችን ፈፅሞው የሌሉ፣ ህዝብ ለህዝብ የሚያጋጩ፣ ሀገሪትዋን ወደባሰ ትርምስንና አደጋ የሚዳርጉ፣ ሃላፊነትና ፓለቲካዊ ስነ ምግባር የጎደለባቸው ብቻ ሳይሆን በስልጣን ላለው ስርዓት የሚጠቅሙና ዱላ የሚያቀብሉ ናቸው።

ለምሳሌ ፅንፈኞቹ አዘውትረው ከሚያናፍሱዋቸው በእውነታ ላይ ያልተመሰረቱ የውሸት ፕሮፓጋንዳዎች ውስጥ **የትግራይ ህዝብና ህወሓት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅ ናቸው ከሚል የተሳሳተ መነሻ ሁሉም ትግርኛ ተናጋሪ የስርዓቱ ደጋፊና ልዩ ተጠቃሚ አድርገው ይመለከቱታል።** ይህ ከእውነታ የራቀ አመለካከት የሚያሳየን አራት ነገሮችን ነው። አንዱ ጠላትና ወዳጅ ለይቶ አለማወቅ ነው። ሁለተኛ በሀገራችን ያለው የተወሳሰበ የፓለቲካ ሁኔታና እውነታ ተንትኖ የማወቅ ዓቅምና ባህርይ እንደሌላቸው ነው። ሶስተኛ በስልጣን ላይ ያለው ስርዓት የሚያነፍሰውን ወሬና የሚነዛው ፕሮፓጋንዳ ሰለባ ከመሆንና እሱ የሚሰጣቸው የቤት ስራ ከመስራት ሌላ የራሳቸው የሆነ የጠራ የፓለቲካ ራእይና ዝግጁነት እንደሌላቸው እንገነዘባለን። አራተኛ ከመንግስት ጋር የሚያጣላቸው ስልጣን እንጂ የህዝብ ጉዳይ እንዳልሆነ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል።

በትግራይ አካባቢው ስላለው ሁኔታ ከህዝቡ በላይ ሌላ ምስክር ሊኖር አይችልም። የትግራይ ህዝብ ዛሬም በጦርነት ቀጠና ስር ሆኖ በሻዕቢያና በህወሓት በሁለት አለንጋ እየተገረፈና መሬቱ በቦምብ እየጋየ እንዳለ፣ ጥቂት የልማት ተቋሞች ቢመሰረቱም የማን ኪስ እየሞሉና እነማን እየተጠቀሙበት እንደሆነ፣ መሪዎቹና አጫፋሪዎቻቸው የህዝብ ሀብት ዘርፈው በአቋራጭ ስለበለፀጉ ጭቁኑ የትግራይ ህዝብ ተጠቅሟል ማለት እንዳልሆነ፣ የተወሰኑ ትግርኛ ተናጋሪዎች በሰራዊቱም ሆነ በቢሮክራሲው አካባቢ ስላሉ የትግራይ ህዝብ ነግሷል ማለት እንዳልሆነ፣ ህወሓት እንደ ድርጅት በሀገርና በህዝብ ሉዓላዊነት ላይ የፈፀመው ክሕደት የትግራይ ህዝብ ተጠያቂ እንዳልሆነ፣ ዛሬም በህዝብ ላይ እየተፈፀመ ያለው አፈናና ጭቆና በትግራይ አካባቢም የባሰ እንደሆነ፣ አንድ አምባ ገነናዊ መንግስት አንዱን ህዝብ ጨቁኖ ሌላውን ህዝብ የመጥቀም ባህርይ እንደሌለውና ያለው እውነታም የሚያረጋግጥልን ይህንን እንደሆነ ተደጋግሞ ተገልፀዋል። ይሁን እንጂ “አህያውን ፈርተው ዳውላውን” እንዲሉ የበላውን ዘራፊ አካል ትተው ያልበላውን ህዝብ በልቷል፣ የስርዓቱን ልዩ ተጠቃሚ ሆኗል፣ ነግሷል፣ የአንበሳ ድርሻ ወስዷል፣ ወዘተ እያሉ የከሰረና የሻገተ ፓለቲካ በማራመድ የንፁህ ህዝብ ታሪክና ክብር ሲያጎድፉ ይታያሉ።

እውነታን መቀበል ያቃታቸው ፅንፈኞች ይህ ብቻ አይደለም በትግራይ ህዝብ ላይ የከፈቱት የጥላቻ ዘመቻ። የትግራይን ህዝብ በስልጣን ላይ ካለው አምባ ገነን ስርዓት ጋር ደርበው ተጠያቂ ለማድረግና ቢቻላቸውም ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር አጣልተው፣ አጋጭተውና ነጥለው ለመምታት የሚያደርጉት የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ የስርዓቱን ካድሬዎች ከሚያነፋሱት ወሬዎች የባሰ እንጂ ያነሰ አይደለም። ለዚህ አብነት የህወሓት መሪዎች ለአገዛዝ እንዲመቻቸው ያደረጉትን የመሬት ድልድል ወልቃይት ወደ ትግራይ ክልል ተወሰደ በማለት ልክ የትግራይ ህዝብ በጎንደርና በወሎ መሬት ላይ እንደ ዘመተ አስመስለው በተለያየ ዜና ሲናገሩ እንሰማለን። የመሬት ጉዳይ ካነሳን ዘንድ ወልቃይት ብቻ አይደለም። የትግራይ ህዝብ ለዘመናት ሲጠቀምበት የቆየ የጨው፣ የእርሻና የማዕድን እምቅ ሀብት ያለበት መሬትም በምስራቅ ትግራይ ወደ አፋር ክልል ተወስዷል። ነገር ግን ፅንፈኞች ዓይናቸው በጥላቻና በጠባብ

አመለካከት ግርዶሽ ስለተሸፈነ ሚዛናዊ ሃሳብ ይዘው "ለዘመናት በትግራይ ክልል የነበረ መሬት ለምን ለአፋር ክልል ተሰጠ?" ብለው ለመጠየቅና ለመናገር አልደፈሩም።

እኔ በሀገሬ በየትም ቦታ መኖር የምችል ኢትዮጵያዊ ነኝ ብዬ በልበ ሙሉነት እስካመንኩኝ ድረስ በክልሎች መካከል የሚደረገው የመሬት ድልድል ብዙ የሚያስጨንቅ አይደለም። ከዚህ የባሰ ሌላ በሀገር ደረጃ መነሳት ያለበት ትልቅ የህዝብ አፈናና ጭቆና እያለ ወደ የመንደር ቁርሾ የምንገባበት ጉዳይ መሆን የለበትም ባይ ነኝ። በስልጣን ላይ ያለው መንግስትም የሚፈልገው ይህንን ነው። ትልቁን አጀንዳ ወደ ጎን ትተን እሱ የቀየሰው የቤት ስራ እየሰራን በጥቃቅን ነገሮች እርስ በራሳችን እተየናቆርን እንድንኖር ነው። ስለሆነም እውነታን መቀበል ያቃታቸው ሀይሎች የሚያራምዱት የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ለትግሉ የሚፈይድ ሳይሆን እኛን በተለያየ ስልት ለያይቶ ለመግዛት እንቅልፍ አጥቶ ለሚያድር ለአቶ መለስ ዜናዊ መንግስት ትልቅ መሳሪያ ሆኖ የሚያገለግል ነው።

ነገር ግን ፅንፈኞች፣ ሌሎች የሻዕቢያ ጀሌዎችና ተባባሪዎቻቸው ያልተገነዘቡት ሁለት መሰረታዊ ነገሮች አሉ። አንዱ መሰረታዊ ጉዳይ የትግራይ ህዝብም ሆነ ሌላ ብሄር ብሄረሰብ አግልሎ፣ አሳንሶ፣ አንቋሽሾና አደናግሮ የስርዓት ለውጥ ሊመጣ አይችልም። በሌላ አነጋር የትግራይ ህዝብን ነጥሎ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር አትኖርም ማለት ነው። ሁለተኛ ማወቅ ያለባቸው መሰረታዊ ነገር ትግላችን አንዱን አምባ ገነን አስወግዶ በሌላ ፅንፈኛ፣ ጠባብ፣ ከፋፋይና ቂመኛ አምባ ገነን ለመተካት አይደለም። ዋናው የትግላችን መሰረትና አላማ ለሁላችንም እኩል የሚያገለግል ዲሞክራሲያዊ ስርዓትና ሁላችንም በነፃነትና በፍቅር ተከባብረን የምንኖርባት ሀገር ለመገንባት እንደሆነ ከወዲሁ ሊገነዘቡት ይገባል።

ሌላው እውነታን በመቀበልና ባለመቀበል ዙሪያ ለኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ ለሌላው ዓለም እንቆቁልሽ የሆነው ጉዳይ ኦነግ በኦሮሞ ህዝብ ስም የሚያነሳው የመገንጠል ጥያቄና የሚያራምደው ውጤት አልባ የሆነ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ነው። የኢትዮጵያ ሁኔታ ከኦነግ ጋር ሲነፃፀር በአእምሮ የሚመላለሱ ብዙ ነገሮች አሉ። ብዙውን ጊዜ ወደ ሀገር ቤት ስመላለስ የኦሮሞ ህዝብ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ የተለየ ስሜት፣ አኗኗር፣ የዕድገት ደረጃና መልክ አላየሁም። ጂኦግራፊያዊ አቀማመጡ፣ አሰፋፈሩ፣ ማሕበረ አኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ግንኙነቱ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ጋር በሁሉም ቦታ ከጫፍ እስከ ጫፍ ተሰባጥሮ፣ ተዋልዶና ተዋሃህዶ የሚኖር ህዝብ ነው። በአሁኑ ጊዜ ኦሮሞ የሌለበት የኢትዮጵያ ምድር የለም ቢባል ከሀቅ ውጭ አይሆንም።

ከዚህ እውነታ በመነሳት ለኦነግ ሰዎች ያለው ጥያቄ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር መስርተው የታሪክና የሀገር ባለቤት ከሆኑት ኢትዮጵያውያን አንዱ የኦሮሞ ህዝብ ነው። ታዲያ የመገንጠል ጥያቄ ራስህ የሰራኸውን ቤት መልሶ በገዛ ራስህ ማፍረስ አይሆንም ወይ? ተገንጥሎስ ወዴት ነው የሚሄደው? ያለ ኦሮሞ ህዝብስ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ትኖራለች ወይ? በታሪክስ የኦሮሞ ህዝብ የራሱን ህጋዊ መንግስት መስርቶ የኖረበት ዘመን አለ ወይ? በኢትዮጵያ ውስጥ ጭቆና መኖሩ ማንም የሚክድ ሰው የለም። ነገር ግን የኦሮሞ ህዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ የተለየ ጭቆና ነበረው ወይ? የጭቆና ምንጭስ ማን ነው? ህዝብ ወይስ ገዢ መደቦች? የመገንጠል ጥያቄ እውነት የኦሮሞ ሰፊው ህዝብ አንገብጋቢ ጥያቄ ቢሆን ንሮ ኦነግ ለምን ከሃምሳ ዓመት በላይ ወሰደበት?። በአሁን ጊዜ ኦነግ ከኢትዮጵያውያን ጋር ተማክሮና ተባብሮ የጋራ ችግር በጋራ ከመስራት ይልቅ ከኤርትራ አምባ ገነን መንግስት ጋር ተመሳጥሮና ተባብሮ ኦሮሞን ከኢትዮጵያ ለማስገንጠል እየሰራ ይገኛል። የኔ ጥያቄ እውነት የሻዕቢያ መንግስት ለኦሮሞ ህዝብ ድህንነት፣ ነፃነትና ዕድገት ከኢትዮጵያውያን ወንድሞቹ በላይ የበለጠ ፍቅር፣ ወገናዊ ጥብቅና፣ ታሪካዊ ትስስርና ዝምድና ስላለው ነው? የሚሉና ሌሎች የማያሻማ መልስ የሚሹ የወቅቱ ጥያቄዎች ናቸው።

## ሐ) የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው (የፅንፈኞች የፖለቲካ ቁማር ጨዋታ)

የሻዕቢያ ሕልምና ምኞት የተዳከመች፣ የተበታተነች፣ ዳግም የባህር በር ጥያቄ የማታነሳና ለኤርትራ

ኢኮኖሚ ማዳበሪያ ሆና ዘላለም የምታገለግል ድሃ ኢትዮጵያን ማየት ነው። ይህንን ሕልሙና ምኞቱ እውን ለማድረግ ደግሞ ነፃ አውጪ ነን የሚሉ ሀይሎች በማሰልጠን በማስታጠቅና በማሰማራት ያለ መታከት ሲሰራ ቆይቷል። አሁንም ሳይተኛ ሌት ተቀን እየሰራ ይገኛል። ከዚህም አልፎ በትዕቢት በኢትዮጵያ ላይ ቀጥተኛ የሆነ ወረራ በማካሄድ ሉዓላዊነታችንንና ክብራችንን ተዳፍሯል። በተለይም የትግራይ ህዝብን አድምቷል፣ ቀጥቅጧል፣ ክብሩንና ዳር ድንበሩንም ጭምር ጥሷል። በአሁኑ ጊዜ ሻዕቢያ የኢትዮጵያ ደመኛ ጠላት መሆኑን የማያውቅ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ አለ ብዬ አላምንም። ነገር ግን የሚገርመውና ለኢትዮጵያ ህዝብ እንቆቁልሽ የሆነው ጉዳይ ትንቢተ-ኢሳያስ አፈወርቂ ለኢትዮጵያ መፈራረስና መበታተን የሚመኝ መሆኑን ብቻ አይደለም። አንዳንድ ፅንፈኞች "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው" ከሚል የተሳሳተ ስሌት መነሻ በማድረግ የራሱን ህዝብ መፈናፈኛ አሳጥቶ በሀይል ረግጦ ከሚገዛና የኢትዮጵያ ህዝብን ጥፋት ከሚመኝ የባዕድ ጠላት ጋር በማበር ነፃነትና ዲሞክራሲ እናመጣላችኋለን በማለት እኛን ለማሞኘትና ለማዘናጋት በሀገርና በህዝብ ላይ የሚሰሩት የፓለቲካ ቁማር ጨዋታ ነው። ይህ ድርጊት በኛ በኢትዮጵያውያን ላይ ያላቸው ንቀት የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ ትግላችን ፈር እንዳይዝ አደፍራሽ ሆኖ መገኘቱ ነው።

ከላይ እንደገለፅኩት የኦሮም ህዝብ መገንጠል ምርጫው ቢሆን ኖሮ የኦነግ ሃምሳ ዓመት የዔሊ ጉዞ አያስፈልገውም ነበር። ሻዕቢያ ለኦሮሞ ህዝብም ሆነ ለሌላው ኢትዮጵያዊ ነፃነትና ዲሞክራሲ የሚመኝለት ቢሆን ኖሮ ነጋ ጠባ ታጣቂዎችን እየላከ የትግራይ፣ የአፋር፣ የሱማሌና ሌሎች ክልሎች መሬትና ሂይወት በቦምብ አያቃጥልም ነበር። ለሻዕቢያ ከፅንፈኞች በላይ የበለጠ የሚቀርበው በስልጣን ላይ ያለው ህወሓት/ኢሕአዴግ ነው ምክንያቱም ከማንም በላይ ለኤርትራ ህልውናና ነፃነት የቆመና አሁንም እየታገለ ያለው ስርዓት ነው። እነዚህ ፅንፈኛ ድርጅቶች የሻዕቢያ መንግስት ብቻ አይደለም ለመሳሪያነት የሚፈልጋቸው። የአቶ መለስ ዜናዊ መንግስትም በመጀመሪያ አካባቢ ለኦነግ የአማራ ነፍጠኛ ለመምታት በሚል ስልት ይጠቀምበት እንደነበረ ሁሉ አሁንም ጨርሶ እንዲጠፉ አይፈልግም። ምክንያቱም ኦነግ ለይስሙላ አለ እየተባለ የአቶ መለስ ዜናዊ አገዛዝ ህዝቡንና አባላቱን ለማስፈራሪያ ይጠቀምበታል። ሻዕቢያም በወገኑ ፅንፈኛ ድርጅቶችን ከሚደግፍበት ዋናው ምክንያቶች አንዱ ከአቶ መለስ አስተዳደር ጋር ለመደራደር እንደ ተፅእኖ መፍጠሪያ አድርጎ ለመጠቀም ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ምናልባት በኢትዮጵያ እነሱ ስልጣን የሚይዙበት አጋጣሚ ቀዳዳ ቢፈጠር ሕልሙንና ምኞቱን ለማሳካት ነው።

ስለሆነም ሻዕቢያና ተባባሪዎቹ ፅንፈኞች ሕልማቸውንና ምኞታቸውን ለማሳካት የመጀመሪያ ጠላታቸው የአቶ መለስ ዜናዊ አገዛዝ አይደለም። እንዲያውም በስልጣን ላይ ካለው ገዢው ፓርቲ ተሸማግለው የሆነ ጥቅም ተጋርተው የሚኖሩበት አጋጣሚ ካገኙ ወደኋላ እንደማይሉ በሩ ዝግ አይደለም። በአንፃሩ በኢትዮጵያ እንደ ስትራተጂያዊ ጠላት አድርገው የሚመለከቱት የአንድነት ሀይሉን ነው። በኢትዮጵያዊ ብሄረተኛነት መሰባሰብ ለነ አቶ መለስ ብቻ ሳይሆን ለነሱም በጣም ያስፈራቸዋል። በዚህ መሰረት በኢትዮጵያ የተቀናጀ፣ የተዋሃሃደና ቀጣይነት ያለው ትግል እንዳይኖርና እንዳይጠናከር የመጀመሪያ ዒላማ የሚያደርጉት አንድነት ሀይሉን መጥረግ፣ ማዳከምና ማደናገር ነው። በኔ አመለካከት እነዚህ ሀይሎች ዓቅምና አጋጣሚ ካገኙ ከአቶ መለስ ዜናዊ አገዛዝ የባሱ እንጂ የተሻሉ እንደማይሆኑ ባህሪያቸው፣ አካሄዳቸውና አላማቸው ያስረዳል።

ፅንፈኞች በስልጣን ላይ ያለው የአቶ መለስ አስተዳደር የሚቃውሙት በተግባሩ ሳይሆን ከማይኖሪቲ (አናሳ ብሄረሰብ) ብለው ከሚጠሩት ትግርኛ ተናጋሪ  የመጣ ነው ብለው ስለሚያምኑ ነው። እኔ ግን ይህንን ሃሳብ እቃወማለሁ። እኔ አገዛዙን የምቃወመው በቋንቋው፣ ከአናሳ ብሄር ስለመጣ፣ በቀለሙ ወይም በዘር ግንዱ ስሌት ሳይሆን በተግባሩና በሚያራምደው የተሳሳተ ፓሊሲ ነው። ለወደፊቱም ቢሆን እነ አቶ መለስ ዜናዊ ከስልጣን ሲለቁ የብሄር ብሄረሰብ አባል ያልሆነ ርእሰ ብሄር

ከሰማይ አይመጣም። ፅንፈኞች መመዘኛቸው ቋንቋና ዘር ከሆነ ከየተኛው ወገን ስልጣን ላይ ሲወጣ ነው የሚመቻቸው?። በኔ እምነት ለሁላችን የምትሆን የጠነከረችና የበለፀገች ዲሞክራሲያዊት ሀገር ለመገንባት መመዘኛችን አንዱ የበላይ ሌላው የበታች፣ አንዱ ተጠቃሚ ሌላው የበይ ተመልካች፣ አንዱ የስልጣን ባለቤት ሌላው አጃቢ፣ አንዱ የአንድነት ጠበቃ ሌላው አፍራሽ፣ አንዱ ባለታሪክ ሌላው መጤና ተለጣፊ፣ አንዱ አናሳ ሌላው ደግሞ ግዙፍ አድርጎ በማየት ትልቁ ዓሳ ትንሹን ዓሳ እየበላ እያስፈራራ የሚኖርበት ሁኔታ ሳይሆን ሁላችንም በመከባበር፣ በመፈቃቀድ፣ በመደማመጥ፣ በመቻቻልና በእክልነት ላይ የተገነባ ሀገራዊ አንድነት መስርተን በሰላምና በፍቅር ለመኖር የሚያስችለን ሁኔታ ሲፈጠር ብቻ ነው።

## ማጠቃሊያ

የህወሓት/ኢሕአዴግ ደጋፊዎችና አባላት ሊያጤኑት የሚገባ እውነታ መንግስትና ግለ መሪዎች አላፊ ሀገርና ህዝብ ግን ዘላለም ነባሪ መሆኑን ነው። ጊዜውም የአምባ ገነኖች ዘመን እየከሰመ የነፃነት ጎህ እየቀደደ በመሄድ ላይ መሆኑን ብዙ ጭብጦች ይታያሉ። ይህም ወደ ሌላ ሳንሄድ በዙሪያችን ያለው የህዝቦች መነሳሳት ማየቱ በቂ ይመስለኛል። የቱኒዝያው ቢን ዓሊ፣ የሊቢያው መሐመድ ጋዳፊ፣ የግብፁ ሁሴን ሙባረክና የየመኑ ሳሊሕ አንድ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በህዝባዊ ማዕበል ተጠራርገው ወደ የታሪክ ቆሻሻ ስፍራ ይጣላሉ ብሎ ያሰበ ሰው ብዙም አልነበረም። አምባ ገነኖች በጊዜያቸው የማይገፉ ተራራ መስለው ቢታዩም የህዝብ ማዕበል በተነሳ ቀን ግን መቋቋም እንደማይችሉ በተግባር ታይቷል። <u>ነፃነትና ፍትሕ የጠማው የኢትዮጵያ ህዝብም</u> የጊዜ ጉዳይ እንጂ አንድ ቀን መነሳቱ የማይቀር መሆኑን ጥርጥር የለውም። በመሆኑም ዛሬ ዓለም በሰለጠነበት ዘመን አማራጩ ሰፊ እያለ ነገር ግን የግል ጥቅም ከሀገርና ከህዝብ በላይ በማስቀደም ከጥቂት አምባ ገነኖች ጋር ወግኖ ራሱን የታሪክና የትውልድ ተወቃሽ የሚያደርግ ሰው ማን ነው?

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ አማራጭ ሀይል እሆናለሁ የሚል የፖለቲካ ድርጅት ኋላ ቀር የፖለቲካ ባህልን ሰብሮ መውጣት አስፈላጊ ከሚሆንበት አንዱ ተወዳድሮ ለማሸነፍ ህዝብን ማሳመን የግድ ይላል። አሁን ያለው ትውልድ ደግሞ እንደ ድሮ “ክተት ሰራዊት ምታ ነጋሪት” ተብሎ በስሜት ወይም በጥላቻ የሚነዳ ህዝብ አይደለም። የአንዱን ሃሳብ ለመቀበል ወይም ላለመቀበል በእጅ የሚዳሰስ፣ በተግባር የሚታይ፣ ምክንያታዊና በእውነታ ላይ የተመሰረተ አጀንዳ ይፈልጋል። ዕድሜ ለቴክኖሎጂ ዕድገት ዛሬ ዓለማችን በመረጃ ፍሰት ወደ አንድ መንደር ተሰባስባለች። ህዝቡም በተለይም በውጭ ሀገር የሚገኘው ኢትዮጵያዊ በዓለም ዙሪያ ምን እየተደረገ እንደሆነ ተመኩሮ የመከታተል ዕድል አለው። በሀገር ውስጥም ሕብረተሰቡ በአመለካከትም፣ በንቃትም በተመኩሮም የፖለቲካ ድርጅቶችን አልፎ ብዙ ርቀት ሂዷል። ይህ ሁኔታ ሚዛኑ ካልተለወጠ ደግሞ ኋላ ቀር የፖለቲካ ባህልና ተለምዳዊ አሰራር ተይዞ የሃያ አንደኛ ክፍለ ዘመን የለውጥ አንቀሳቃሽ ኃይል ለመሆን ፍፁም አይቻልም።

በማጠቃለል የጋራ ችግር በጋራ ለመፍታት ተባብረን እንስራ ስንል ለአንድ የምርጫ ወቅት ብቻ ተሰባስበን በማግስቱ የሚፈርስ ዕድር እናቋቁም ማለት አይደለም። ለ85 ሚሊዮን ህዝብና ለነገው ትውልድ የሚዘልቅ፣ በጠራ አላማና እውነታ ላይ የተመሰረተ ራእይ ይዘን በቁርጠኝነት ለመስራት በሕብረት እንነሳ ማለታችን ነው። ሰሞኑን በዜና ማስራጫዎች ከኦነግ አንዱ ክንፍ ፕሮግራሙን አስተካክሎ ከኢትዮጵያውያን ጋር አብሮ ለመስራት ወሰነ የሚል ጥሩ ዜና ተሰምቷል። እውነት የኦነግ አባላት ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች በማጤንና አጥሩን ሰብረው በመውጣት ወደ ትክክለኛው የትግል መስመር ተመልሰው ከሆነ እሰዬው የሚያሰኝ አዲስ የትግል ምዕራፍ ከፋች ነው። ሌሎቹም ይህንን አርአያ እንዲከተሉ የሁላችን ጥረትና በጎ ምኞት መሆን ይኖርበታል በማለት ሃሳቤን እቋጫለሁ፡፡

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!!

ኢሜይል sgbtsait@gmail.com